# Sani Tweaks (ሳኒ ትዊክስ)



የንጽህና/ለጤና መልካም ልምዶች

የታተመው በኦክስፋም GB  ለኦክስፋም ኢንተርናሽናል በ

ISBN 978-1-78748-381-1 in ታህሳስ 2018. DOI: 10.21201/2018.3811 ስር

ኦክስፋም GB፣ ኦክስፋም ሀውስ፣ ጆን ሲሚዝ ድራይ፣ ኮውሊ፣ ኦክስፎርድ OX4 2JY, UK

© ኦክስፋም ኢንተርናሽናል ታህሳስ 2018


---


ይህ ስእላዊ የእጅ መጸሀፍ የሳኒ ትዊክስ ተከታይ ነው፡ በሽንት ቤት እና በንፅህና ፕሮግራሞች ውስጥ የተሻሉ ልምዶችን ለማስተዋወቅ የሚውሉ የግንኙነት መሣሪያዎች

**www.oxfam.org.uk/sanitweaks**

# የመመሪያው ተግባር


ጥናቶች እንዳሳዩት ኤጀንሲዎች/ድርጅቶች የሚገነቧቸው መጸዳጃ ቤቶች ተጠቃሚዎችን በተገቢው መንገድ የማያማክሩ ወይም አስተያየቶችን /ግብረ መልስን ከተጠቃሚዎችበመሰብሰብ እርምጃ የማይወስዱ ሆነው ተገኝተዋል - በተለይ ሴቶችና ልጃገረዶችን - መጸዳጃ ቤቶቹ ተደራሽ ባለመሆን፣ የማያገለግሉ እና/ወይም ደህንነታቸው ያልተረጋገጠ በመሆኑ መጸዳጃ ቤቶቹን መጠቀም አቁመዋል። ስለሆነም በድንገተኛ አደጋ ግዜ የጤና ስጋቶችን በህብረተሰቡ ላይ የሚፈጥር/ከፍ ያለ እንዲሆን ምክንያት ሆኖ ተገኝቷል።





ይህን ለማስተካከል፣ የኦክስፋም የውሃ የመጸዳጃ እና የጤና ባለሙያዎችቡድን (WASH TEAM) ምርጥ የሆነ የንጽኅና አጠባበቅን ለማስተዋወቅና በዘርፉ አለማቀፋዊ የሆነ መመሪያን ለማቅረብ ተከታታይ የሆነ የመርጃ  መሳሪያ አዘጋጅቷል




ከሳኒ ትዊክስ የማረጋገጫ ዝርዝር የወጣ ሲሆን የሚከተለው ስእላዊ ገለጻ ቴክኒካዊ የፊልድ ሰራተኛ ለማሳወቅ፣ ተጠቃሚዎችን እንዲያማክሩ/እንዲዳምጡ ለማገዝ/ለማበረታታትና በንድፋቸው ላይ ቀጣይ የሆነ ማሻሻልን እንዲያደርጉ ነው።

**ይህ ትንሽ “ትዊክስ/ማሻሻያ” ሴቶች መጸዳጃ ቤትን እንዲጠየሙ ወይም እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ ትልቅ ልዩነት ፈጣሪ ነው።**


# የሰገራ ማስወገድ (የሽንት ቤት አቅርቦት) ቀጣይነት ያለው አገልግሎት  እንጂ የአንድ ግዜ ግንባታ/አገልግሎተ አይደለም

ብዛት ባላቸው የመጸዳጃ ቤት ፕሮግራሞች/አቅርቦቶች በተሰራ የቅርብ ጥናት እንደሚያሳየው ከሆነ 40% የሚሆኑ ሴቶች በቀረቡ መጸዳጃ ቤቶች አይጠቀሙም።

## ቀዳሚ ምክንያቶች




መጸዳጃ ቤቱ በተገቢው ቦታ አለመሆን




ነጻነት ማጣት (ተደብቆ የሚጠበቅ ሰው እንዳያይ በመፍራት)




ጾታዊ ጥቃትን መፍራት



በምሽት ብርሀን አለማግኘት



ተገቢ ቁልፍ በበር ላይ አለመኖር



ነፍሳትን መፍራት


“ **የመጸዳጃ ቤትን መጠቀም የሚያስደስተኝ** ማንም እንዳይገባ በሩን መቆልፍ ስችል ነው ። ንጽህናው የተጠበቀ መተላለፊያና በመንገዱም መብራት እንዲኖረው እፈልጋለው። ንጽህናው የተጠበቀና ከነፍሳት የጸዳ መሆኑም ለኔ ወሳኝ ነገር ነው። ”



መጸዳጃ ቤቱ ጥቅም ላይ ካልዋለ ገንዘብ፣ ግዜና ሀብት ይባክናል _በዚህም ምክነያት አብረነው ስንሰራ ለነበረው ማህበረሰብ ሀላፊነታችንን አልተወጣንም ማለት ነው። ይህም በከፍተኛ ደረጃ በየሜዳው መጸዳዳትና ሌሎች አማራጮች የሚያስከትል ሲሆን ይህም ሰዎችን ህመም ላይ በመጣል የጤና ችግር ስጋትን ያሳድራል።




በምሽት ወደ መጸዳጃ ቤት መሄድ ሴቶች በካምፕ ውስጥ ከሚያደርጉችው አደገኛ ነገሮች አንዱነው።



የጊዜ እጥረት ለዝቅተኛ ጥራት ያላቸው መጸዳጃ ቤቶች ወይም የህብረተሰቡ ምክክር አለመኖር እንደ ምክንያት አይሆንም።

## ለሴቶች መንደፍ፣ ከሴቶች ጋር

ለሁሉም የተሻለ እና የተጠቃሚውን ደህንነት የሚያረጋግጥ  አገልግሎት መስጫ/ተቋም  እንዲሆን ያግዛል።




“ **የመጸዳጃ ቤትን መጠቀም የሚያስደስተኝ** ስገባና ስወጣ የማልታይ ሲዎን ነው፡፡ ውስጥ በምሆን ግዜ ነጻነቴን እፈልጋለሁ፡፡ በበሩ ወይም በግድግዳ ቀዳዳ መታየት አልፈልግም፡፡ ”




# በእያንዳንዱ ሂደት ተጠቃሚዎችን ማማከርና ማሳተፍ ያስፈልጋል።



ልጆችን መስማት



ሴቶችንና የደረሱ ልጃገረዶችን መስማት



ወንዶችን መስማት



**“ የመጸዳጃ ቤትን መጠቀም የሚያስደስተኝ** በቀንም ሆነ በምሽት በውስጥ የማደርገውን ነገር ማየት ሲቻለኝ ነው። ለልጄና የአካል ጉዳት ላለባት እናቴ አስባለሁ። በመጸዳጃ ቤት ውስጥ ለእናቴና ለክራንቿ ቦታ እንዲኖረው እፈልጋለሁ እንዲሁም ቀዳዳው ለልጄ በትክክለኛው መጠንም መሆን አለበት። ”



# ወሳኝ ጥያቄዎችን መጠየቅ

## በጣም ተገቢ/ቁብል የሆነውን መጸዳጃ ቤት ለመገንባት

**በውይይቱ ላይ ሴቶችና ወንዶች እኩል ተሳትፎ አላቸው?**

ባህላዊ ልማዶችና መቀመጫን የማጽዳቱ ዘዴዎች ምንድናቸው?

---

ሃይማኖታዊ ልምዶች ምንድን ናቸው?

በፊት ምን ያደርጉ ነበር እንዲሁም የአሁኑ ልምዳችውስ እንዴ ነው?

---

ተቀባይነት ያላቸው ሌሎች አማራጮች አሉ?

የህዝብ ወይም የጋራ መፀዳጃ ቤቶችን ለመጠቀም ዋናው ችግር ምንድነው?

**ያስቡ:**

- ቦታ?
- ነጻነት?
- ጥቃት?
- መብራት/ብርሀን?
- ቁልፍ?
- ከሌሎች ጋር መጋራት?

በምሽት ሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞችና አዋቂ ሰዎች ምን ያደርጋሉ?

---

ለ 24 ሰአት አገልግሎትእንዲሰጥ ምን አይነት አማራጮች ቀርቧል?

መጸዳጃውን የተለያዩ ቤተሰቦች መጋራት ይችላል? የማይተዋወቁ ከሆነስ?

---


ከሆነ፣ ለወንድና ለሴት የተለያየ መጸዳጃ ቤት ያስፈልጋል?


በወንድና በሴት መጸዳጃ ቤት መሀል ተቀባይነት ያለው ዝቅተኛው ርቀት ምን ያህል ነው?





# በተግባራዊነት ላይ ያተኮረ ውይይት

## ከማህበረሰብ ጋር









### ቦታና ንድፍ

የመጸዳጃ ቤቱ የሚሰራበትን ቦታ ሲወሰን ተጠቃሚዎችን ማሳተፍ።።

ከተቻለ፣ ለሙከራ የተሰራና ስእሎችን ለተጠቃሚ በማሳየት ንድፍ ላይ ሀሳብ /አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ።።

### ጥገና

የጋራ መጸዳጃውን የማጽዳትና የመጠገን ሀላፊነት የማን እንደሆነ ከግምት ማስገባት?

ማሃንዲሶች ና የጤና ባለሞያዎች **ለአጭር** እና **በረጅም** ጊዜ በጣም ተገቢ የሆነውን የጥገና ስትራቴጂ መወሰን እና ርክክብን ከግምት ውስጥ **ማስገባት**አለባቸው።።

### እጅ መታጠብ

ተጸዳድተው ከጨረሱ በኋላ ተጠቃሚዎች እጃቸውን በውሃ እና ሳሙና እንዲታጠቡ ለማድረግ የተሻለው ዘዴ ምንድነው?

### ተግባራት

መጸዳጃ ቤቱ እንዴት በፍጥነት እንደሚሞላ፣ ሲሞላ እንዴት ባዶ እንደሚሆንና ሰገራው የት እንደሚወገ ከግምት ማስገባት።።


# በንድፍ/በዲዛይን ወቅት ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው

- ደህንነት
- ነጻነት
- ተደራሽነት
- የወር አበባ ንጽህና አያያዝ (MHM)
- እጅ መታጠብያ



# ደህንነት






## ብርሃን/መብራት

ሰዎች ወደ መጸዳጃ ቤት ሲሄዱ/ሲመለሱ እንዲሁም ውስጥ ሆነው ደህና መሆናቸው ለማረጋገጥ በጣም ተገቢ የሆነው የብርሃን ምንጭ/መብራት ምንድነው?

አምፖል በሚሰቀል ግዜ ጥላ እንዳይፈጥርና የተጠቃሚውን ጥላ  በውጭ በኩልእንዳያሳይ አድርገው ሊሰቅሉ ይችላሉ?



## ቁልፎች


በድንገተኛ/በአስቸኮይግዜም ቢሆን እንኳ የሚሰራ የውስጥ ቁልፍ አለ? ከፍታው ለአዋቂዎችና ለልጆችን ምቹ ነው?



## ቦታና ተደራሽነት

**ርቀት፣ ደህንነት ፧ግልጽ መዳረሻ፣ ነጻነት አስብ።**


ቦታው ሴቶች ወደ መጸዳጃ በሚሄዱ ግዜ ደህንነት እንዲሰማቸው ያደርጋል? (መጸዳጃ ቤቱ ከመኖሪያ ቦታ በ 50 ሜትር ርቀት ውስጥ መሆን ያለበት ሲሆን ነገር ግን በጭራሽ በተጨናነቀ መንገድ ላይ መሆን የለበትም።)




## አከባቢዎች

እባብና ነፍሳትን ለማስወገድ በአካባቢው ያሉ ቁጥቋጦዎችን ማጽዳት።


# ነጻነት






## የግድግዳ ከፍታ/ቁመት

የመጸዳጃ ቤቱ ከፍታ ነጻነትን ሙሉ ለሙሉ ለማጎናጸፍ
የሚያስችል ከፍታ አለው?ምቹ/በቂ ነው



## የግድግዳ መስሪያ እቃ


ላስቲክ ለጥቅም ከዋለ፣ ውስጥ ያለን ሰው ሊያስይ ይችላል?
የተቀደደ ቦታ ካለው መፈተሽና አስፈላጊ ከሆነም መጠገን።




## በር/በሮች

**ያስቡ፡**
በበሮቹ መሀል ክፍተት አለ?
የተጠቃሚው እግርና ጭንቅላት አይታይም?
በተገቢው ሁኔታ የሚገጥም ቁልፍ አለው?

# ነጻነት






## ወንድ/ሴት መለየት


የወንድና ሴት መጸዳጃ ቤቶቹ አንዱ ከአንዱ በቂ ርቀት አላቸው? ጀርባ ለጀርባ መሆን በጭራሽ የለባቸውም።

መለያው ግልጽ መሆንና በማህበረሰቡ በቀላሉ የሚለይ ነው?



## የተለያየ መግቢያ


የመጸዳጃ ቤቶች እንዴት መቀመጥ ወይም መለየት አለባቸው በመሆኑም ሰዎች ወደ መጸዳጃው ሳይታዩ መግባት ይችላሉ?




## መመልከቻ

ተጠቃሚዎች መመልከቻ ከፈለጉ፣ ምን አይነትና ቅርጽ እንደሚመርጡ መጠየቅ።

# ተደራሽነት






## የውስጡ ቦታ/ስፋና የበር ስፋት

ከልጅ ወይም ድጋፍ ከሚያስፈልገው የቤተሰብ አባል ጋር መግባት ለሚፈልግ ሰው በቂ ቦታ በክፍሉ አለ?




## አካል ጉዳተኛና አረጋውያን

ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰቡ አባላት እንቅፋቶች አሉ?



## ሕጻናት

ተገቢነት ያለው ተቋም/መጸዳጃ ቤት ለመንደፍ ወንድና ሴት ልጆችን ማማከር።



**ህፃናትና ጨቅላዎች፡**
የትንንሽ ህጻናትን ሰገራ ለመሰብሰብና ለማስወገድ ደህና/ጥሩ መንገድ አለ?

**ቀዳዳ**
የቀዳዳው መጠን ጥሩ/ተገቢ ነው? ሽፋንስ አለው?


# የወር አበባ ንጽህና አያያዝ (MHM)



## ማማከር


**ሴቶችንና ልጃገረዶችን አሁንእያደረጉት ስላለው ነገር ማናገር።**

ተቀባይነት ያለው ነገር ለነሱ ምነድነው? እኛ ልናቀው የሚገባ ነገር ይኖር ይሆን?



## መልሶ መጠቀም


ሴቶች የወር አበባ መጠበቂያ ቁሳቁሶቻን እንዴት አጥበው እንደገና መጠቀም ይችላሉ? ይህ ለማጠብ የሚሆን ቦታ አለ? **የሚደርቁበት** ቦታ/መንገድስ አለ?




## ቆሻሻ ማስወገጃ

የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ሲቀርብ አስፈላጊ የማስወገጃ ሲስተም መሟላቱን ማረጋገጥ።


# እጅን መታጠብ






## አስፈላጊ/መሰረታዊ ነገሮች

ሳሙናና ውሀ ያገኛሉ? ቀጣይነትስ እንዴት ይኖረዋል?



## የእጅ መታጠቢያው ዓይነት/ቦታ

ለማህበረሰቡና ለሁኔታው የእጭ መታጠቢያው አይነት ና ዘዴው /መፍትሄው ተገቢ ነው?




## አነቃቂዎች/ማበረታቻዎች


ከተጸዳዱ በኋላ እጅ መታጠብን እንዴት ማበረታታት ይቻላል?

ቀለማት፣ መስተዋት፣ ማስታወቂያና የእግር መርገጫ ምልክቶችን ያስቡ።

# በመጠቀሚያ ወቅት ና በጥገና  ግዜ መወሰድ ያለባቸው/ አያያዝ








## ማቀድ


የተጠቃሚዎቹን ቁጥር በመያዝ፣ ጉድጓዱ በምን ያህል ግዜ እንደሚሞላ አስልተውታል? ለማስመጠጥ/ለመድፈን አቅደዋል?

## ጥገና

በወር ውስጥ አብዛኛው የፕላስቲክ ሸራ ይበላሻል። መጸዳጃ ቤቱ በስራ ላይ መሆኑን ለማረጋገጥ መደበኛ የሆነ ቁጥጥርና ጥገና ያስፈልጋል።







## ማስመጠጥ

ለማስመጠጥ ከታቀደ ጉድጓዱ በቀላሉ ቱቦ ማስገቢያ አለው? ወለሉ ይከፈታል?

## የመጸዳጃ ቤት ማጽጃ እቃዎች

የመፀዳጃ ቤት ማፅጃ  እቃዎች መሰራጨት እና በተገቢው ጥቅም ላይ መዋሉን ያረጋግጡ። በቤተሰቦች መካከል እንዴት በጋራ ይጠቀማሉ?

## ግብረ መልስ/አስተያየት


ብልሽትን ወይም የንድፍ ችግርን ለሚያሳውቁ እንዲሁም ግብረ መልስ የሚሰጡብት ምን አይነት ሲስተም/መንገድ ጥቅም ላይ ይውላል? ሲስተሙ ላልተማሩት ጨምሮ ለሁሉም ተደራሽ መሆኑን ማረጋገጥ።



“ **መጸዳጃ ቤቶችን በመጠቀም ደስታ የሚሰማን** እኛ ስንደመጥ ና የሚያሳስበን ነገር በአስተማማኝ ሁኔታ ተሰሚ ሲሆን ነው። ”

መፀዳጃ ቤቶቹ ከተጠቃሚዎች አስተያየት ጋር እንዲስማሙ እና የተስተካከለ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ተደራሽ የሆኑ ተቋማትን መኖሩን ለማረጋገጥ በፕሮጀክቱ ሂደት ውስጥ ሁሉን አቀፍ የህብረተሰቡ ምክክር መኖሩ ወሳኝ ነው።

ኦክስፋም ከዘላቂ የንፅህና አጠባበቅ ህብረት ጋር በመተባበር፣ ኦክስፋም ለዘርፉ ጥቅም የተሻሉ የንፅህና አጠባበቅና አሰራሮችን ለማስተዋወቅ ይህንን  መርጃ አዘጋጀ። የቀረበው ለሁሉም ኤጀንሲዎች/ድርጅቶች በግለሰብ ፍላጎቶች መሠረት እንዲሰሩ እና እንዲጠቀሙት ለማገዝነው።



OXFAM

sustainable sanitation alliance